Week 7

Grade 2

# አዛውንቱ መንገደኛ



Leveled

# አዛውንቱ መንገደኛ

Leveled | Grade 2 | Week 7



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2008 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ወቅቱ በጋ ነው፤ የቀትር
ፀሐይ እንደእሳት ይፋጃል።



አዛውንቱ መንገደኛ ብዙ
ልብሶችን ደራርበው ለብሰዋል።



ከናቴራ፣ ሸሚዝ፣ ሹራብ፣
ጋቢና ካፖርት ለብሰዋል።



አዛውንቱ ሙቀቱን መቋቋም አልቻሉም።



ላባቸው በግንባራቸው ቁልቁል ይወርዳል።



አዛውንቱ በመጀመሪያ ካፖርታቸውን አወለቁና መጓዝ ጀመሩ።



ሙቀቱ ያው ነው፤

በመቀጠል ጋቢያቸውን

አወለቁ።



ጋቢያቸውን በራሳቸው፣
ካፖርታቸውን በትከሻቸው
ያዙ።



የፀሐይዋ ሙቀት ሊቀንስ
አልቻለም፤ ጋቢያቸውንና
ካፖርታቸውን በእጃቸው ያዙ፡፡



ፀሐይን ቀና ብለው ተመለከቷት፤ የፀሀይ ጨረር ዓይናቸውን ወጋቸው።



አንገታቸውን ደፉ፤ ሹራባቸውን አወለቁ::



ጥላ ፍለጋ አማተሩ። አንድ ዛፍ በሩቅ ታያቸው፤ ፈገግ አሉ።